# ጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ከተማ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ያዘጋጁት ሕዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁናቴ ተጠናቀቀ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በአውሮፓ ባጠቃላይ በተለይም በጀርመን ሀገር ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ጋር በመገናኘት የሚያደርገውን ድርጅታዊ ተግባር በመቀጠል ባለፈው ቅዳሜ ነሐሴ 18 ቀን 2005 ዓ. ም. (ኦገስት 24 ቀን 2013 ዓ. ም.) በፍራንክፈርት ከተማ እንዲሁ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት ያደረገው ውይይት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።







በቅድሚያ በስብሰባው አዘጋጅ የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ ሊቀመንበር በሆኑት በጓድ ሰለሞን አማካኝነት የስብሰባውን ተካፋዮች በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ከከፈቱ በኋላ በመቀጠል ላለፉት 40 አመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ሲታገሉ ለወደቁት ወገኖቻችን የአንድ ደቂቃ የሕሊና ፀሎት እንዲደረግ በጠየቁት መሰረት የፀሎት ዝግጅቱ ተከናወነ። በማስከተልም የኢሕአፓ የማንነት

መግለጫ የሆነው “የትግሉ ነው ሕይወቴ“ የተሰኘው መዝሙር በክራር እየታጀበ በደመቀ




ሁኔታ ተዘመረ።

በመቀጠል ሕዝባዊ ውይይቱ በወጣቷ እህታችንና የኢ.ሕ.አ.ፓ ደጋፊ ኮሚቴ አባል በወይዘሪት መቅደስ ሰፋ ባለ ሁኔታ ባጣቃላይ ሴቶች ኢትዮጵያዊያን በተለያየ ደረጃ በወያኔ አገዛዝ እየደረሰባቸው ያለውን በደልና አልፎ ተርፎም ኑሯቸውን ሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ባልሆነ ደረጃ በአረብ ሀገራት በተሰደዱ በርካታ ሴት ኢትዮጵያዊያን ላይ ስለሚደርሱት አሳዛኝ ሰቆቃዎች ከገለጹ በኋላ ይህንን የእህቶቻችንን ፍዳ ላንዴና ለዘለቄታው እንዲገታ ለማድረግ አያት ቅድመ አያቶቻችን ባወረሱን የነፃነት ወኔ መርህ ላይ በመመርኮዝ በጋራ እንድንታገል ጥሪ በማቅረብ ገለፃቸውን ደምድመዋል።



በማስከተል የኢ.ሕአፓ ወጣት ክንድ አባል የሆኑት ወጣት ይርጋ „ለምን እኛ የኢ.ትዮጵያዊያን ወጣቶች የወያኔ አገዛዝን እንቃወማለን?“ የሚል ጥያቄ በማስቀደም ካቀረቡ በኋላ መልሳቸውንም ወያኔ ቃል ገብቶ ነገር ግን ሊፈፅም ያልቻለውን በርካታ ቃሎችን በዝርዝር ከጠቀሱ በኋላ በተለይም የተለያዩ አገዛዞች መሰሪ ተንኮል ያዘለ አምባገነናዊ ስርአታቸውን ለማስፈንም ሆነ አገዛዝቸውን ለማስፈፀሚያን ለማጠናከሪያ በወጣቱ ትውልድ ላይ ትኩረታቸውን እንዴት እንደሚያደርጉ የጀርመንና የጣሊያን ፋሺስታዊ ፓርቲዎችን፡ ከቀድሞ ሶሻሊታዊ አምባገነን አገዛዞች ከምስራቅ አውሮፓ እንዲሁም ወደ ኤሽያ ዘለቅ ብለው በቬይትናም ኢንዶኔዢያ፡ በቻይና የተደረጉትን ምንጊዜም ሊረሱና ከሰው ሕሊና ሊጠፉ የማይችሉ የተለያዩ ምሳሌዎችን ከታሪክ በማጣቀስ በስፋት አብራርተዋል። በማያያዝም የወያኔ አገዛዝም ቢሆን የነሱን ፈለግ ተከትሎ በሀገራችን ተግባራዊ እያደረገ ያለው ፖሊሲ የተሳሳተ በመሆኑ በወጣቱ ትውልድ ላይ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ በሕዝባችን እየደረሰ ያለውን በደልና ጭቆና የዚሁ ውጤት እንደሆነም ገልፀዋል። በሀገራችን ከተገኘው ተምክሮም በመነሳት የወያኔ አገዛዝ ገና ከጥንሥሱ ጀምሮ ብቻ ሳይሆን ሥልጣን ከጨበጠ ጀምሮም ላለፉት 21 አመታት ድረስ




ሳይቀር ታሪክ ያቀረበለትን ፈተና ሊወጣ ያልቻለ ቡድንና በዚህም መውደቁን አብራርተዋል። ወጣት ይርጋ በመቀጠል በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ “የኢ.ትዮጵያዊያን ወጣቶችም የወያኔ አገዛዝን አጥብቀው መቃወም እንደሚገባቸው“ ከጠቆሙ በኋላ በተለይ ወጣት ሴቶችና ወንዶች የኢ.ሕአፓ ወጣት ክንድን እንዲቀላቀሉ የከበረ ጥሪያቸውን በማቅረብ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

የሚቀጥለው ተናጋሪ የኢሕአፓ የበላይ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑት ዶ/ር ዘነበ ተሾመ ሲሆኑ እሳቸውም በበኩላቸው የድርጅታቸው የትግል ዋልታ ስለሆኑት ስለ ሶስቱ እሴቶች ማለትም „የግለሰብ ነፃነትና እኩልነት፤ በወንድማማችነት/ እህትማማችነት“ መርህ ላይ የተመረኮዘ መተሰሰባን




ያነገበማህበረሰብ ለመመስረት በሚደረገው ትግል ከሀገር አንድነትና ከሕዝባዊ እኩልነት ጋር በማዛመድ ሰፋ ያለ ገለጻ ከሰጡ በኋላ ለወጣቱ በተለይ ስለ ነፃነት እኩልነትና ወንድማማችነት አስመልክቶ የፖለቲካ ንቃታቸውን እንዲያሳደጉ የከበረ ጥሪያቸውን በማቅረብ ገለፃቸውን ደምድመዋል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ፕሬዘዳንት የሆኑት የተከበሩ አሊ ሁሴን በበኩላቸው ስለ ድርጅታቸው መቼና ለምንስ እንደተመሰረተ በስፋት ለተሰብሳቢው ከገለፁ በኋላ ድርጅቱ በተለያዩ ጊዜያት ስላደረጋቸው ተግባራትና ስላስገኘው መልካም ውጤት በመዘርዘር ኢትዮጵያዊያን ድርጅታቸውን በተለያዩ መልኮች እንዲቀላቀሉና እንዲረዱ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ስሜትና የሚቀሰቅሱ ግጥሞችን በማንበብ የውይይቱ ተካፋዮችን አዝናንተዋል።




የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ሊቀመንበር የተከበሩ አሊ ሁሴን በጀርመን ሀገር የሚገኙ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ለድርጅታቸው እስካሁን ድረስ እያደረጉ ያሉትን የተለያዩ እርዳታዎች በማመስገን ሌሎች ኢትዮጵያዊያንም ይህንን ፈለግ እንዲከተሉና ከድርጅታቸው ጋር ግንኙነት ለማድረግ ለሚፈልጉ ሁሉ ዋና መቀመጫው በበርሊን ከተማ እንዳለ ገልፀው አድራሻውንም ሊያገኙ እንደሚችሉ ገልፀዋል።

በፕሮግራሞቹ መካከል በክራር የታጀቡ የተለያዩ ዘፈኖችን አርቲስት እንዳለ ጌታነህ (ባሻ አሸብር) ያቀረቡ ሲሆኑ ከዚሁ ጋርም በበኩላቸው ያቀረቡት ግጥምም የተሰብሳቢውን ልብ የማረኩ መሆናቸው ከተሰብሳቢው ለማወቅ ተችሏል።

በመጨረሻም የጥያቄና መልስ ውይይት ከተደረገ በኋላ የስብሰባው ተካፋዮችም በበኩላቸው በቀረበው ዝግጅት መርካታቸውንና መሰል ዝግጅት እንዲደረግ ፍላጎታቸውን በመግለጽ ከአዘጋጁ ክፍልም በሚቀጥለው ጊዜ ለየት ባለ መልክ ተመሳሳይ ዝግጅት በለሎች ከተሞች እንደሚያዘጋጅ ቃል በመግባት የቀኑ ትዕይትንት ተገባዷል።

